በወታደራዊው መንግሥት ዘመን ለነበረው የፖለቲካ ሥርዓት ታማኝነት የነበራቸውና ሌሎችም በወሬና በአሉባልታ ጊዜአቸውን ይፈጁ የነበሩ ሰዎች አባቴን ከቤተ ክርስቲያኒቱ የበላይ ኃላፊዎችና ከመንግሥት ባለሥልጣናት ፊት ለመክሰስ የሚቀድማቸው አልነበረም። በዚህም ምክንያት በነዚሁ ሰዎች በሚያቀርቡበት ክስ የተነሣ በተደጋጋሚ ወደ አገሪቱ የደኅንነት ቢሮ እየተጠራ ይቀርብ ነበር። ለአገር ሰላምና ለቤተ ክርስቲያን የነበረውን ጥልቅ ፍቅር፣ ይልቁንም ደግሞ ከማንም ሊሰወር የማይችለውን መንፈሳዊ ሰብእናውንና እውነተኛነቱን ይረዱ የነበሩ የሥራ ኃላፊዎች በአብዛኛው በከፍተኛ አክብሮት ይመለከቱት ስለ ነበረ ብዙ ሊጎዱት አይደፍሩትም ነበር። በደኅንነት ቢሮ ውስጥ ይሠሩ ከነበሩ ኃላፊዎችም ውስጥ ለበላዮቻቸው ተአማኒ በአባቴ ላይ መጥፎ ነገር እንዳይደርስበት ከለላ የሚያደርጉለት ሰዎችም ነበሩ።



# ምዕራፍ ፭
# ሃያ የተጋድሎ ዓመታት
# ፲፱፻፷፯ -፲፱፻፹፭

## አባቴና የፍኖተ መስቀሉ ዋዜማ

አገራችን ኢትዮጵያ ከወታደራዊ መንግሥት ወደ ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት በተረማመደችበት ወቅት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ነበሩ፡፡ የመንግሥት ለውጥ ከተደረገ በኋላ፤ ሳይውል ሳያድር፤"በጤና ማጣት ምክንያት ሥልጣኔን ለቅቄአለሁ" ብለው ከመንበራቸው ወረዱ ተባለ፡፡ በወቅቱ "ሕመምን እንደ ምክንያት ተጠቀሙበት እንጂ ሥልጣናቸውን እንዲለቁ ግፊት ስለ ተደረገባቸው ነው" እየተባለ በስፋው ተወርቷል፡፡

ፓትሪያርኩ ይህን ውሳኔአቸውን ሲያሳውቁ በጊዜው የነበረው ቅዱስ ሲኖዶስም ለጥያቄአቸው ድጋፍ ሰጥቷል፡፡ እንደ ሊቃውንት ጉባኤ ኃላፊነቱ አባቴ ይህንን ውሳኔአቸውን በጊዜው በተደረገው ስብሰባ ላይ አጥብቆ መቃወሙን ለተለያዩ ቃለ መጠይቆች በሰጣቸው መልሶች ገልጿል፡፡ ፓትሪያርኩ ሕመምና ድካም ካገኘው እንደራሴ መሠየም እንደሚችል በሕገ ቤተ ክርስቲያን የተፈቀደ በመሆኑ ይሄንኑ መሠረት በማድረግ ነበር አባቴ የብፁዕ ፓትሪያርኩን ውሳኔ የተቃወመው፡፡

እሱ ያንን ተቃውሞ ሲያቀርብ ጉዳዩን ይመለከት የነበረው ከሕገ ቤተ ክርስቲያን፥ ከክብረ ቤተ ክርስቲያንና ፓትሪያርኩ ሲሾሙ ከገቡት ቃል ኪዳን አንጻር እንደ ነበረም በተለያዩ ጊዜአት ተናግሯል፡፡ፓትሪያርኩ ከአገር ከወጡ በኋላ ከመንግሥት በደረሰብኝ ጫና ምክንያት ነው የለቀቅኩት ማለታቸውን በሚመለከት በእርሳቸው ደረጃ ከሚገኝ አባት እንደዚህ ያለ ነገር መነገሩ አግባብ አለመሆኑን ገልጿል፡፡

"አንዲት መንበር ለተሾመባት አባት እንደ ሕጋዊ ሚስት የምትቈጠር ናትና ስለ ቤተ ክርስቲያንና ስለ ሕዝበ ክርስቲያን ክብር ሲሉ እስከ መሥዋዕትነት እንኳ ቢፈለግባቸው ተገቢውን ዋጋ መክፈል ነበረባቸው፡፡ እኛም አብረናቸው እንሰለፍ ነበር" በማለት በጉዳዩ ላይ የነበረውን አቋም በግልጽ አሰምቷል፡፡

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትሪያርክ አባ መርቆሬዎስ ሥልጣን ከለቀቁ በኋላ መንበረ ፓትሪያርኩ በዐቃቤ መንበር ለአንድ ዓመት ያህል ቆየ፡፡ ከዚያም ፓትሪያርክ አባ ጳውሎስ ፭ኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ ተብለው ተሾሙ፡፡

የወታደራዊው መንግሥት ዘመን ከተፈጸመ በኋላ ከሀገረ አሜሪካ የተመለሱት አባ ጳውሎስ አወዛጋቢ በሆነ የምርጫ ሂደት አልፈው ፓትሪያርክ፣ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ዕጨጌ ዘደብረሊባኖስ፣ ንቡረዕድ ዘአክሱም ተብለው በመጠራት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በበላይነት መምራት ጀመሩ፡፡

ፓትሪያርክ አባ ጳውሎስ የተመረጡበት የምርጫ ሥነ ሥርዓት በመንበረ ፓትሪያርኩ ግቢ በተከናወነበት ቀን አባቴ ወደ ቤተ ክህነት ግቢ አልሄደም ነበር፡፡ ከምርጫው ዋዜማ ጀምሮ ተደጋግመው በተደረጉ የስልክ ጥሪዎችና እቤታችን ድረስ በመጡ ሰዎች አማካይነት በምርጫ ሥነ ሥርዓቱ ላይ ተገኝቶ እንዲመርጥ የሚያሳስቡ ተደጋጋሚ ጥያቄዎች ቀርበውለት እንደ ነበረ በዚያን ዕለት እቤት ውስጥ ስለ ነበርኩኝ ለመታዘብ ችያለሁ፡፡ ስልክ ቢደወልም መኪና ቢላክም እሱ ግን አልሄደም፡፡ በዚያን ዕለት ስለነበረው ሁኔታ ግንቦት ፲፩ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. የወጣው መብሩክ ጋዜጣ አባቴን አነጋግሮት ነበረ፡፡ እሱም፣

“እኔ ሳልሆን ያለሁበትን የሥራ ክፍል የሚጠይቅ በመሆኑ ብቻ እንደ አንድ ሰው ድምጽ እንዲሰጥ ተመዝግቦ ኖሮ...አለቃ መኰንን ግብረ መድህን (በዚያን ጊዜ የአስተዳደር ክፍል ሃላፊ የነበሩ) መጥተው ትፈለጋለህ እንሂድ አሉኝ፡፡ ጉዳዩን ጠየቅኋቸው፡፡ የሊቃውንት ጉባኤ ድምጽ የሚሰጥበት አንተን የሚጠብቅ ስለሆነ እዚያ እንሂድና ካርዱን ወደ ቦታው መጨመር አለብህ አሉኝ፡፡ አልሄድም አልመርጥም ብያቸው ቀረሁኝ፡፡ ...” በማለት ተናግሯል፡፡

፭ኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትሪያርክ የነበሩት ፓትሪያርክ ዶ/ር አባ ጳውሎስ ለዘመናት የጳጳሳት መለያ

በዝርዝር አብራርተው ነገሩኝ፡፡ ከዚህ በመነሣት እሁኑኑ የቀዶ ጥገናውን ከማድረግ የተሻለ አማራጭ እንደማይኖር፥ ምንም እንኳ ጉዳቱ ከባድ ቢሆንም፤ ሕክምናው ግን በቀላሉ መሠራት የሚችልና ቶሎ የሚድን መሆኑን ገለጡልኝ፡፡ ይህንኑ ለአባቴ አስረድቼ እንዳሳምንና የእሺታ መልስ እንዳመጣላቸው ሌላ ቀጠሮ ሰጥተውኝ ተለያየን፡፡

ከፕሮፌሰር ቢሮ እንደ ወጣሁኝ ቀጥታ የሄድኩት አባቴ ወደ ተኛበት ክፍል ነበር፡፡ አባቴ ሕክምና ለመቀበል ብዙም ደስተኛ እንዳልሆነ ከድሮ ጀምሮ የማውቅ በመሆኔ ነገሩን ማንሣት አስፈራኝ፡፡ ከፕሮፌሰር ዐሥራት መልእክትና ከአባቴ ዘላቂ ጤንነት አንጻር ሳየው ግን በግድ አባቴን ማነጋገር ነበረብኝ፡፡ በመሆኑም እሳቸው ያስረዱኝን መሠረት በማድረግ፤ በይበልጥም ደግሞ ሕመሙ ድጋሚ ሲከሰት በድንተኛ ሁኔታ የሚመጣ በመሆኑ እዚህ ሐሳብ ላይ አጽንኦት ሰጥቼ ነገርኩት፡፡ እሱ ግን ራሱን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ከመስጠት ውጪ ሌላ ተጨማሪ ሕክምና ማድረግ እንደማይፈልግ አጠንክሮ ነገረኝ፡፡ እንዲያውም ይሄን ሀሳብ በድጋሚ እንዳላነሳ አስጠነቀቀኝ፡፡

ለፕሮፌሰር በገባሁት ቃል መሠረት መልሱን መንገር ነበረብኝ፡፡ የእሳቸውን ጭንቀት ድጋሚ ማየት በጣም አስፈራኝ፡፡ ሆኖም ግን መልሱን መንገር ነበረብኝ፡፡ ወደ ፕሮፌሰር ዐሥራት ቢሮ ተመልሼ ሄድኩኝና ስለሁኔታው ነገርኳቸው፡፡ በጣም አዘኑ፡፡

" እሳቸው መኖር ባያጓጓቸውም እኔ መኖራቸውን በጣም እፈልገዋለሁ፡፡ እኔም ብቻ ሳልሆን በጣም ብዙዎች የእሳቸውን መኖር ይፈልጉታል፡፡ ለኢትዮጵያና ለቤተ ክርስቲያን ሲባል የእሳቸው ዕድሜ መርዘሙ በጣም አስፈላጊ ነው" አሉኝ፡፡

የምለው ጠፍቶኝ ዝም ብዬ አንገቴን አቀረቀርኩኝ፡፡ በሰላማዊ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ሲናገሩ የሚያስደስተውና የሚመቸው አንደበታቸው፤ እንዲያ በቅሬታ ተውጠው ሲናገሩበት ከእያንዳንዱ ቃል ጀርባ ከባድ ነገር መኖሩን ያስገነዝባል፡፡ ከስታራ ገጽታቸው የተመልካቹ ልብ



በአክብሮት እንዲፈራቸው የሚያስገድድ ግርማ አለው፡፡እኔ አክብሮቴንና ፍርሃቴን በዝምታ ላሰላስል፤እሳቸው ንግግራቸውን ቀጠሉ፡፡

"ዛሬ እኔ ሥራዬ ላይ እያለሁ የምችለውን ብረዳቸው ደስ ይለኝ ነበረ፡፡ ምን አልባት ድጋሚ ታመው ሲመጡ እኔን ላያገኙኝ ይችላሉ፡፡ ቀን ቀንን ሲወልድ ምን እንደሚፈጠር አይታወቅም" አሉኝ፡፡ በዚያን ዘመን እሳቸው የመኢሕድ ሊቀ መንበር ስለ ነበሩ አንዳች የሚሠጉበት ነገር መኖሩን ለመገንዘብ አልከበደኝም፡፡

ተስናብቻቸው ከቢሯቸው ስወጣ የአባቴ የጤንነት ሁኔታ የፈጠረብኝን ሥጋት፤ እሳቸው ላይ ያየሁትን ለአገርና ለወገን የመጨነቅ ስሜት፤ እንዲሁም ስለመጪው ጊዜ የተሰማቸው ስጋት ውስጤን በጣም ረብሾት ነበረ፡፡ ያም ሆነ ይህ አባቴ ሁለተኛው የቀዶ ጥገና ህክምና ሳይደረግለት ከዐሥራ አምስት ቀናት የሆስፒታል ቆይታ በኋላ ወደ ቤት ተመለሰ፡፡ ከዚያም አንድ ወር ያህል ዕረፍት አድርጎ ወደ ቢሮ መሄድ ጀመረ፡፡

የአዲሱ ፓትሪያርክ "አዲስ የአመራር አቅጣጫ" በሃሳብ የሚመስሏቸውን ብቻ ይዞ መጓዝ በመጀመሩ የሚሠራው ሥራ ሁሉ ነባሩን የሊቃውንት ጉባዔ ያገለለ ነበረ፡፡ አባቴ ስለ ቫቲካኑ ጉዞ ያነሳው ጥያቄ ያስቆጣቸው ፓትሪያርኩ ቁጣቸው ሊለቃቸው ስላልቻለ እንኳን ለጥያቄው መልስ ለመስጠት በሌሎች ጉዳዮች ላይ ለማነጋገር ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ ሁኔታው በዚህ ላይ እንዳለ አባቴ እንደገና ታመመ፡፡

ሐምሌ ፩ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. አባቴ ሥራ አልሄደም ነበር፡፡ በዚህ ቀን የምሥራቅ ጎጃም ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አባ ባስልዮስ ወደ አባቴ መጥተው ስለ ቫቲካን ጉዞ ያቀረበው ጥያቄ የፈጠረውን ቅሬታ ለመፍታት ጥረት በማድረግ ላይ ነበሩ፡፡ የአባቴና የሊቀ ጳጳሱ ንግግር የእርስ በርስ መከባበር የሰፈነበት ነበረ፡፡ አባቴ ስለ ቫቲካን ጉዞ ያቀረበውን ጥያቄ በቀላሉ እንዲያየውና እንዲተወው፡፡ በተጨማሪም ስለአነሳው ጥያቄ ፓትሪያርኩን ይቅርታ ጠይቆ እንዲታረቅ አጥብቀው ለመኑት፡፡

*በደሙ የማሌትን መሐላ አፍርሰው የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን የሮም ቅኝ ግዛት ስላደረጉ፤ ፍርድ ይሰጥልን!» ሲሉ በጎያሉ አምላክ አቤቱታ አቀረቡ።ከዙፋኑ የመጣው መልስግን፤ «እስከ ዕለተ ምጽአት ፍርድ የቤተክርስቲያን ነው!» የሚልነበረ።ይህ ሁሉ በሚከናወንበት ጊዜ የማላውቀው ኀይል ከዚህ ዓለም ነጥቆ ከቅዱስ ቁርሎስ ጎን አሰልፎኝ ከቆየ በኋላ ከዙፋኑ የመጣው ድምፅ፤ «አንተ ያየኸውን፣ የሰማኸውን ለቤተክርስቲያን፣ ለምእመናን ንገር!» ሲል አዝዞ ወደነበርኩበት መለሰኝ።"*

በዚሁ ዕለት ቀትር ላይ ከሰመመን የነቃው አባቴ ከኦፕራሲዮን ክፍል ወጥቶ ሦስተኛ ማዕረግ ውስጥ በተገኘለት አልጋ ላይ ተኝቶ ነበር፡፡ ከሰመመኑ ከነቃ በኋላ ብዙዎቹ የቤተሰብ አባላት ወደ ቤት ሲመለሱ አብሬው ቆይቼ የማስታመም ተራ የኔ ነበር፡፡ ስለ ጤንነቱ የሚሰማውን ስሜት ለማወቅ አልፎ አልፎ ለምጠይቀው ጥያቄዎች መልስ ከመስጠት ውጪ አብዛኛውን ሰዓት በዝምታና ጠሰድ መለስ በሚያደርግ የእንቅልፍ ስሜት ውስጥ ሆኖ ሰዓቱ መሸ፡፡ ወደ ማታ ላይ ስሜን ጠርቶ መኖሬን ካረጋገጠ በኋላ

"ዛሬ ቀን ስንት ነው?" ብሎ እንደ ጠየቀኝ፡፡

"ሐምሌ ፳ ቀን ነው፡፡" አልኩት፡፡

"ግሩም ነው" ብሎ ዝም አለ፡፡

«ኮሎስቶሚ» እንደ ተሠራለትና ኮሎስቶሚውን ለመዝጋት ሌላ ሦስተኛ የቀዶ ጥገና እንደሚያስፈልገው ያወቀው በማግስቱ ሐኪሞች እየዞሩ ሕመምተኞችን በሚጎበኙበት ሰዓት ነበር፡፡ በሁኔታው ቢያዝንም ሌላ አማራጭ አልነበረም፡፡ ከተወሰኑ ቀናት ቆይታ በኋላ ከሆስፒታል ወደ ቤት ተመለሰ፡፡ በታኅሣሥ ወር በ፲፱፻፺፮ ዓ. ም. ላይ የመጨረሻውን ሕክምና እስኪያገኝ ድረስ በሕክምና ዕረፍት ላይ ቆየ፡፡

